የ6ኛ ክፍል አማርኛ ት/ት የ2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

I. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

--------1. ከሚከተሉትአንዱ ቅፅል ነው፡፡
ሀ. አንዲት ለ. ደካማ ሐ. ጨካኝ መ. ለናሐ መልስ ናቸው

-------2. "ሄኖክ" ኳሷን መታ፡፡ "በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ተባቢውን ለዩ፡፡
ሀ. ሄኖክ ለ. ኳሷን ሐ. መታ መ. መልስ የለም

------3. አብዛኛውን ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ በቅንጅቱ መጨረሻ ላይ የሚውለው -------- ነው፡፡
ሀ.ባለቤት ለ. ተሳቢ ሐ. ግስ መ. ሁሉም

------4."የእሱ እርሳስ" በሚለው ሀገር ውስጥ አገናዛቢ ተውላጠ ስሙ ----------- ነው፡፡
ሀ. እርሳስ ለ. የእሱ ሐ. የእኔ መ. መልስ የለም

------5. በአንድ ዐገፍተ ነገር ውስጥ ባለቤቱን ተከትሎ የሚመጣ ቃል -------- ይባላል፡፡
ሀ.ሀረግ ለ. ተሳቢ ሐ. ግስ መ. መልስ የለም

------6. ---------- ገንዘብ እንዳስቀምጥለት ሰጠኝ፡፡ በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ክፍት ቦታውን ሊያሟላ የሚችል ቃል
ሀ.እኛ ለ. እሱ ሐ. እሷ መ. እነሱ

------7. በስም ፊንታ ተተክለተው የማገቡ ቃላት ሁሉ ------- ይባላሉ፡፡
ሀ.ዓ.ነገር ለ. ተውላጠ ስም ሐ. ግስ መ. መልስ የለም

-----8. ከግስ በፊት እየገቡ ግስን ከጊዜ፣ከቦታ፣ ከሁኔታ ወዘተ አንፃር የሚገልፁ---------- ይባላሉ፡፡
ሀ.ባለቤት ለ. ተሳቢ ሐ. ተውሳከ ግስ መ. መ/የለም

-----9. አንድን ስም ከአመልካቹና ከተመልካቹ ቅርበትና ርቀት አኳያ የሚጠቀሙ ------- ናቸው፡፡
ሀ.ጠቋሚ መስተፃምር ለ. ወደረኛ መስተፃምር ሐ. ተውሳከ ግስ መ.ባለቤት

-----10. ተመሳሳይና ተመጣጣኝ የሆኑ ነገሮችን ወይም ድርጊቶችን የሚያጣምሩ -------- ይባላሉ፡፡
ሀ.ግስ ለ. ወደረኛ መስተፃምር ሐ. ተሳቢ መ. ሁሉም

-----11. "በተሰቦቻችን" በሚለው ቃል ላይ የገባው ቅጥያ----------- ነው፡፡
ሀ. ዎች ለ. ኦች ሐ. ኣችን መ. ለና ሐ መልስ ናቸው

II.በ"ሀ" ስር ለተዘረዘሩት የስርዓተ ነጥቦች ስም በ"ለ"ስር ከተዘረዘሩት ተግባራቸው ጋር አዘምዱ፡፡

"ሀ"	"ለ"
----------12. ድርብ ሰረዝ	ሀ. በዓረፈተ ነገሩ ውስጥ የጥያቄ ሀሳብ መኖሩን ያመለክታለ
----------13. ነጠብጣብ	ለ. ሀሳቡ ከሌላ የተወሰደ መሆኑን ያመለክታል
----------14. ትምህርተ ጥቅስ	ሐ. መገረምን፣መደነቅን...ወዘተ ለማመልከት ያለመክታል
----------15. ትምህርተ አንክሮ	መ. የቀረ ሀሳብ መኖሩን ለማመልከት ያገለግላል
----------16. ጥያቄ ምልክት	ሠ. ድርብ ሀሳቦችን አጣምሮ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡

III.ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ፃፍ፡፡

17. እምር አመልካች ቅጥያዎችን ከስም ጋር በማጣመር ስሙን እምር አድርጉ /በሶስቱም ቅጥያዎች ሶስት እምር የሆነ ቃል ፃፉ፡፡
18. "በላሀ" የሚለው ቃል ስንተኛ መደብ ነው?
19. "እፅዋት ህይወት ያላቸው እንደ እንስሳት ሁሉ ናቸው"፡፡የሚለውን ዐረፍተ ነገር አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡
20. "አስተዳደግ -ዋ- ም" የሚለውን ቃል አጣምራችሁ ፃፉ፡፡

የ6ኛ ክፍል ሳይንስ የ2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

I.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ለሆነው "እውነት" ትክክል ላልሆነው "ሀሰት" በማለት መልሽ

-----------1.አጥቢዎች የወተት እጢዎች ያሏቸው ኢ-ደንደሴ እንስሳት ናቸው፡፡

-----------2.በሀገራችን ከሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት ዝርያ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እንቁራሪት አስተኔዎች ናቸው፡፡

----------3.የዱር እንስሳት ከፊል ተፈጥሮአዊ ምቹጌ ብሔራዊ ፖርክ ይባላል፡፡

----------4.እንቁላል ጣይ ዶሮዎች ከበደ የሰውነት ክብደተ አላቸው፡፡

----------5.አንድ አካል ለማየት ብርሃን ከአካሉ ተንፀባርቆ ወደ አይናችን መግባት አለበት፡፡

II.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ፃፍ፡፡

--------6. ከሚከተሉተ ውስጥ አጥቢ እነስሳት የሆነው

ሀ. ዶሮ   ለ. ጭልፊት   ሐ. የሌሊት ወፍ   መ. እባብ

-------7. በስፋቱ ትልቅ የሆነው ብሔራዊ ፖርክ --------- ነው፡፡

ሀ.ነጭ ሳር   ለ. ባሌ ተራራ   ሐ. ሰሜን ተራራ   መ. ጋምቤላ

-------8. ከሚከተሉተ የአይነ ክፍሎች ዘንጌና ቅንብቤዎች የሚገኙበት --------------

ሀ. እውሬ ነጥብ   ለ. ነርብ እይታ   ሐ. እይታ ድራብ   መ. ሀ እና ለ

-------9. የአይን ቅርፅን የሚጠብቅ ክፍል -------------- ነው፡፡

ሀ.ማዕሰረ ሌንስ   ለ. ዝልግልግ ፈሳስ   ሐ. ብሌን   መ.ሌንስ

-------10. ስለ ብርሃንና እይታ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ --------- ነው፡፡

ሀ.ስነ-በሲር   ለ. ማይክሮስኮኘ   ሐ. ቴሌስኮኘ   መ.ፔሪስኮኘ

------11. የብርሃን ጨረሮች ስብስብ ብለው ሲጓዙ --------- ይባላሉ፡፡

ሀ.የብርሃን ጨረር   ሐ. እርፍ ጨረር

ለ. ቅልስ ጨረር   መ. የብርሃን አመልማሎ

------12. ከሚከተሉት አንዱ ብርሃንን ያስተላልፋል፡፡

ሀ.አየር   ለ. ውሃ   ሐ. ምስሪት   መ. ሁሉም

------13. ብርሃን ከዝቅተኛ በሲራዊ እፍግታ ወደ ከፍተኛ በሲራዊ እፍግታ ሲጓዝ /ሲገባ/ ቅልሰቱ

ሀ.ይቀንሳል   ለ. ይጨምራል   ሐ. እኩል ይሆናል   መ. መልስ የለም

-------14. በየትኛው ብርሃን አንፀባራቂ መስታወት አካሉ ከአምሳሉ በእኩል ርቀት ይገኛል፡፡

ሀ. በሰርጉድ መስታዎት   ሐ. በእብጥ መስታዎት

ለ. በዝርግ መስታዎት   መ. ሁሉም

III.ለሚከተሉት ጥያቄዎች በ"ለ" ምድብ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች ከ"ሀ" ምድብ በመምረጥ አዛምድ/ጅ/ ፡፡

------15. ስርጉድ መሰታዎት   ሀ. ጨረሮች ተኮልኩለው የሚሰበሰቡበት ነጥብ

------16. ፔርስኮኘ   ለ. እውነተኛ እና የተዘቀዘቀ ምስል

------17. እብጥ መስታዎት   ሐ. እውናዊ ቀጥያለ ከመስታወቁ ጀርባ የሚፈጠር

-------18. የኩርበት ማዕከል   መ. ከወለል በታች ሆነው ከወለል በላይ የሆነን ነገር የሚታይበት

------19. ትክተታዊ ነጥብ ሠ. ምስሪቱን መሀል ለማህል የማያቋርጥ መስመር

-------20. የምስሪት ዋልታዎች ረ. አብይ ዘነጉ የሚያልፍባቸው የምስሪቱ ሁለት ገፆች ማዕከል

-------21. አብይ ዘንግ ሰ. የትክበታዊ ርዝመት እጥፍ ርቀት ነው፡፡

የምዕራፍ አምስት የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ.ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. ብራንፊ ውስጣዊ የዓይን ክፍል ነው፡፡
2. የሩቅ እይታ የዓይን ኳስ ትልቅ ሲሆን የሚከሰት ችግር ነው፡፡
3. በዓይን ውስጥ አምሳል የሚፈጠረው በእይታ ድራብ ላይ ነው፡፡
4. ሥርዓተ ነርቭ የህዋስ ነርቭ ትንሹ አካል ነው፡፡
5. የወንድ ነባዘር የሚመረተው እንቁልጢ ውስጥ ነው፡፡

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን ምረጡ፡፡

1. ብርሃንን እየመጠነ ወደ ሌንስ የሚያሳልፍ የዓይን ክፍል __ ይባላል፡፡

   ሀ. እይታ ድራብ ለ. ነጭ ድራብ ሐ. ብራንፊ መ. መጣኔ ብርሃን

2. ከሚከተሉት ውስጥ የዓይን እክል ያልሆነው?

   ሀ. የሩቅ እይታ ለ. የአይን ብዥብዥታ ሐ. የቅርብ እይታ መ. ግላኮማ

3. የቀዳማይ አንጎል ንዑስ ክፍል ያልሆነው?

   ሀ. አንጎለ አዕምሬት ለ. አንጎለ ገቢር ሐ. ታላመስ መ. መልስ የለም

4. ስለ ሰረሰር ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የማዕከላዊ ስርዓተ ነርቭ ክፍል ነው

   ለ. የቅጽበታዊ ድርጊት ማዕከል በመሆን ያገለግላል

   ሐ. በአከርካሪ አጥንት ውስጥ ተሸፍኖ ይገኛል መ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ውስጥ ቅጽበታዊ ድርጊት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ማስነጠስ ለ. መብላት ሐ. ማዳመጥ መ. መሮጥ

6. በደም ውስጥ የስኳር መጠን ሲጨምር እንዲቀንስ የሚያደርግ ሆርሞን ምን ይባላል?

   ሀ. ግሉካጎን ለ. ኢንሱሊ ሐ. አድሬናሊን መ. ታይሮክሲን

7. ከሚከተሉት ውስጥ ኢ-መሠረታዊ መፍልኤ ያታ ያልሆነው?

   ሀ. ቆለጥ ለ. የድምፅ መጎርነን ሐ. የጡት ማጎጥጎጥ መ. የወር አበባ መታየት

8. በወር አበባ ኡደት ከሚታዩ ክስተቶች ትክክል ያልሆነው የትኛ ነው?

ሀ. የእንቁላል ከእንቁልጢ መለቀቅ/መውጣት ሐ. የማህፀን ግድግዳ መፈራረስ

ለ. የዳሌ መስፋት መ. አነስተኛ ደም መታየት

9. ከሚከተሉት የአባላዘር በሽታዎች ውስጥ በወቅቱ ካልታከሙት የልብ፣ የአንጎል፣ የዓይንና የአጥንት ጉዳት የሚያስከትለው የትኛው ነው?

ሀ. ጨብጥ ለ. ቂጥኝ ሐ. ከርክር መ. ሁሉም

10. ከሚከተሉት ውሰጥ የአይን ውጫዊ ክፍል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የአይን ቆብ ለ. ሌንስ ሐ. ብራንፊ መ. ብሌን

11. ከሚከተሉት ውሰጥ ብርሀን ከይ አካላት የትኛው ነው?

ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. የዳህራይ አንጎል ተግባርን ዘርዝሩ፡፡
2. በቅጽበታዊ ድርጊት ሂደት መልዕክት በአውደ ቅጽበት እንዴት እንደሚተላለፍ ቅደም ተከተሎችን ግለፁ፡፡
3. አደንዛዥ እፆችን መጠቀም ምን ምን ችግሮችን እንደሚያመጡ አብራሩ፡፡
4. ያልተፈለገ እርግዝናን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ግለፁ፡፡
5. የነጭ ድራብ ብርሃን አስተላላፊ ክፍል ምን ይባላል?
6. አንድን አካል በአይናችን ለማየት የምንችለው ምን ሲሆን ነው?

2nd semester English Work sheet for Grade 6

I. choose the best answer the given alternatives

------------1. Their grandson---------gone missing.

A. have B. has C. having D. is

------------2. Her uncle's---------punished me.

A. has B. having c. have D. are

------------3. I last ------to the cinema two weeks ado

A. gone B. going C. went D. go

------------4. We have -------this workbook since the beginning of term

A. used B. use C. using D. uses

------------5. We have ended ---------term to day

A. my B. our C. his D. her

------------6. They ------ us good stories everyday.

A. tells B. telling C. tell D. told

------------7. I-------- a movie last night.

A. watch B. watched C. watches D. watching

------------8. He --------- a sack of teff and went to home yesterday.

A. carrieyed B. carried C. carries D. carrying

------------9. Some one ---------the chair last Monday.

A. broken B. breaks C. break D. broke

----------10. I used to play foot ball when I was young but now I---------

A. do B. don't C. am D. used to

----------11. The man is my father's brother. He is my ------------

A. grandfather B. aunt C. cousin D. uncle

------------12. Prevention is ------than cure.

A. good B. best C. better D. more good

------------13. London is the ------city in the world.

A. most beautiful B. more beautiful C. beautiful D. less beautiful

------------14. Girma is not as-------- as Hailu.

A. tallest b. tall c. taller D. none

------------15. Both recommendations --------acceptable.

A. are B. is C. was D. has been

------------16. All my neighbors except zewditu ---------gone for the holiday.

A. is B. was C. have D. has

------------17. We shall work very hard,-------we shall get good jobs.

A. but B. to C. and D. since

------------18. The cattle keepers are----------a big number of animals.

A. keep B. keeping C. keeps D. kept

------------19. There isn't ---------thing we can do .

A. some B. a few C. any D. many

------------20. We can prevent soil erosion--------- being washed away.

A. under B. at C. from d. under

II. Passage

Read the following passage and do the questions that follow

Pele was born on October 23,19 40 in brazil . he began his professional career with Santos, football club in 19 56 , which won nine champion ships between 19 58 and 19 69.

In 19 58 in his first world cup appearance, led Brazil to victory .19 70 was his final world cup in which brought victory for brazil. In 19 74 he signaled his retirement from football by picking up the ball 20 minutes in to final game and kneeling in midfield. Between 19 56 and 19 74 peel scored a total of 1,220 goals . He scored five goals in a game six times, four goals. 30 times and three goals 90 times in all international matches.

A. comprehension questions

--------21. Pele began his professional with

A. santos football club in 19 58 B. santos football club in 19 56

C. santos football club in 19 70 D. santos football club in 19 69

--------22. Between 19 58 and 19 69 santos won

A. five championships B. four championships

C. nine championships D. ten championships

---------23. In 19 58 pele led brazil to

A. defeat in the world cup B. victory in the world cub

C. second rank in the game D. third rank in the football match

---------24. 19 70 was the year pele showed his interest to
A. begin to play for santos B. be his final in the world cup
C. retire from playing foot ball D. participate on the next world cup

--------25. Between 19 56 and 19 74 pele scored a total of
A. 14, 000 goals B. 15, 000 goals C. 16, 000 goals D. 1,220 goals

B. vocabularies

26. Career paragraph ___1___ line ___1___ means
A. skill of playing foot ball B. occupation C. first play D. training

27. Victory paragraph line------means
A. appearance B. first match c. defeat of an opponent D. loss

28. scored: paragraph -----------line -----------means
A. last B. reappeared C. gained D. defeated

III. using has /have complete the sentences correctly

29. She (see) the women.
30. We (enjoy) the music.
31. I (throw) it away.
32. They (build) the house.
33. Hanna (speak) to the head teacher.

VI. Complete the sentences with the appropriate possessives of the words given in the brackets

34. We have brought--------------baskets for sale. (we)
35. He has done-------------- work (he)
36. The book is -------------- (my)
37. She has listened to ---------aunt (she)
38. They have paid for --------cousins (they)

I. Choose the best answer from the given alternatives .

--------1.The teacher------------- punish when we did wrong.
A. Used to B. used C. used to D. none

-------2. ------will you go to Paris to visit your uncle?
A. What B. Where C. When D. Which

-----3. There ------- some students in the class room
A. Was B. were C. are D. B and C

-----4. Max is --------- than his brother.
A. Tall B. taller C. more taller D. most taller

------5. Shift ------------- in the Marathon last year.
A. Participated B. participates C. participating D. none

-------6. ------------- is a type of dairy products.
A. Onion B. pumpkin C. butter D. salad

------7. Her uncle ---------- my dress.
A. Has forgot B. have forgotten C. have forgot D. has forget

-----8.The past participle form of draw is -------------

A. drew B. Drawing C. drawn D. none

------9. A: -------------------------.

B: I live in Jimma

A. Where have you been? C. Who take you to Jimma?

B. Why do you come here? D. Where do you live?

-----10. She ----------- to church every Sunday.

A. Go B. went C. goes D. gone

-----11. ----------- You ever seen Merkato?

A. Has B. Have C. Did D. Had

---------12. ----------- child is playing over there.

A. His B. Him C. He D. All

-----13. A: Have you gone to the market?

B: -----------------------------

A. No I haven't gone to the market

B. Yes, I have go to the market.

C. Yes, I have gone to the market.

------14.The book is ----------------

A. my B. mine C. me D. I

--------15.There is a rich man, ----------- he is not happy.

A. Or B .and C. but D. none

-------16. I ---------- killed a lion.

A. Have B. have killed C. have seen D. All

--------17.All students said that Addis Ababa is -------------- capital city.

A. Ours B. us C. me D. our

-------18.He ------------ a new car yesterday.

A. Buys B. bought C. buy D. buying

-------19.----------- child is playing over there.

A. His B. Him C. He D. all

-------20.Their camel has --------------- a lot of heater.

A. Drank B. drunks C. drunk D. drinking

II. Use the following nouns to compete the blank space

- Uncle - nephew - cousin
- niece - grand mother

21. Your brother's sister is your ----------------------
22. Your father's father is your ------------------------
23. Your brothers son is your --------------------------
24. Your uncle's son is your ---------------------------
25. Your father's brother is your------------------------

III. Match Adjectives in "A" column with their opposites under "B column.

የ6ኛ ክፍል 2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

“A”	“B”
--------26. Short	A. rough
--------27. Dirty	B. old
-------28. New	C. clean
-------29. Clever	D. long
-------30. Smooth	E. Lazy
	F. disciplined

GOOD LUCK

General messages:

You should do this work sheet properly!!!

Keep yourselves from Corona Virus!!!

የ6 ክፍል ሒሳብ ት/ት የ2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

ስም --ክፍል ---------ቁጥር -----

I.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክል የሆውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በሉ።

----------1.ትልቁ ኔጋቲቭ ድፍን ቁጥር 0 ነው።

----------2. ማንኛውም ፖዘቲቭ ድፍን ቁጥር ከሀሉም ኔጋቲቭ ድፍን ቁጥር ይበልጣል።

----------3. ዜሮ ከማንኛውም ኔጋቲቭ ድፍን ቁጥሮች ናቸው።

----------4. 0፣1፣2 3………. ፖዘቲቭ ድፍን ቁጥሮች ናቸው።

---------5. ለማንኛውም ድፍን ቁጥር ጠ፣ - (ጠ) = ጠ ነው።

----------6. ወ ድፍን ቁጥር ቢሆን ፣ወ-1 ቀዳማይ ድፍነ ቁጥር ነው።

II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ አማሪጭ የያዘውን ፊደል ፃፍ።

----------7.ትንሹ ፖዘቲቭ ድፍን ቁጥር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 0 ለ.1 ሐ.-1 መ.2

---------8. የሁለት ተቃራኒ ቁጥሮች ድምር ስንት ነው?

ሀ.1 ለ.0 ሐ.0 መ.5

[illegible] ክፍል [illegible] መልመጃ ጥያቄዎች

--------9. የ16 ተቃራኒ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.-16 ለ.16 ሐ.8 መ.-8

--------10. የ-4 ቀዳማይ የቱ ነው?

ሀ.-3 ሐ.3 ሐ.-5 መ.5

-------11. -7 +-(5) ---------- ሀ.12 ለ.2 ሐ.-12 መ.-2

------12. ሸ - 5 8 የ"ሸ" ዋጋ የሆው የቱ ነው ?

ሀ.3 ለ.13 ሐ.-3 መ.-13

------13. 23 -ሸ 20 የሸ ዋጋ የሆነው የቱ ?

ሀ.20 ለ.-20 ሐ.3 መ.-3

-----14. ሸ - 2 7፣ሸ ድ የ "ሸ" ዋጋ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ.9 ለ.10 ሐ.11 መ.8

III. አዛምዱ

ሀ	ለ
-------15.ሩቤ I	ሀ. (3፣ -5)
-------16. ሩቤ II	ለ. (-3፣ -5)
-------17. ሩቤ III	ሐ. (-3፣ 5)
-------18. ሩቤ IV	መ. (3፣ 5)
	ሠ. (0፣ 5)
	ረ. (5፣ 0)

<u>IV.የሚከተሉትን በቁጥር መስመር ላይ አስሉ፡፡</u>

19. -6+-2

20.-2+6

21. ሸ ሙ

22. ሸ +3 -3 ሸ ድ

ትዕዛዝ አንድ፡- <u>በተሰጠው ዓ.ነገር ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ "ሐሰት" በማለት መልሱ</u>

------23. ነጥብ (-3-3) ሩብ III ውስጥ ይገኛል፡፡

------24. 5 + 7ሸ +2ሸ -3+6 = 9ሸ +8

-----25. ሸ - 2 < 0 እና 2 - ሸ > 0 ተመሳሳይ ፍች አላቸው፡፡

----26. (0, 2) በቀጥታ መስመር ቀ = 2ሸ +2 ላይ ይገኛል፡፡

----27. ሸ + < 4 መስሪያ ክልሉ መቁጠሪያ ቁጥር ቢሆን እውን ሰብሰቡ {4,5,6,7 . . . } ነው

ትዕዛዝ ሁለት፡- <u>ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ፃፉ</u>

-----28. , ወ = 3፣ዘ = -2 ፣ ጠ = 2 ቢሆኑ ውጤቱ ---------------------

ሀ. 3 ለ. -3 ሐ. 15 መ. -15

-----29. ቀ ሸ ቢሆንና ሸ 2 ሲሆን ቀ = ቢሆን ሸ = 4 ሲሆን ቀ = ------------

ሀ. ለ. ሐ. 4 መ. 1

-------30. አንድ ከረጢት ከረሜላዎች ይዟል፡፡ ለ10 ህፃናት እኩል ሲካፋፈል እያንዳንዳቸዉ 4 ከረሜላዎች ይደርሳቸዋል፡፡ ለ8 ሕፃናት እኩል ቢካፈል ስንት ስንት ከረሜላዎች ይደርሳቸዋል?

ሀ. 6 ለ. 5 ሐ. 3 መ. 4

--------31. ሸ = 12 ቢሆን የ "ሸ" ዋጋ

ሀ. 16 ለ. 8 ሐ. 9 መ. 12

--------32. ከሚከተሉት ጥንድ ቁጥሮች በ "ቀ" ውቅር የሚገኘው የቱ ነው?

ሀ. (-1,-1) ለ. (2, 2) ሐ. (0 , 8) መ. (8 , 0)

---------33. መስመራዊ የእኩልነት ዓ.ነገር "ቀ = 2ሸ - 4"ን እውነት የማያደርግ ጥንድ የቱ ነው?

ሀ. (4,4) ለ. (-2, -6) ሐ. (0 , -4) መ. (½ , -3)

---------34. የ5 ሜትር ጨርቅ ዋጋ 160 ብር ቢሆን ተመሳሳይ ጥራት ያለው 20 ሜትር ጨርቅ ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?

ሀ. 640 ለ. 320 ሐ. 460 መ. 800

-----------35. ሸ < 4 በሙሉ ቁጥሮች የመስሪያ ክልል ዕውን ስብስቡ

ሀ. {0,1,2,3} ለ. {0,1,2,3,4,5} ሐ. {7,8,9 . . . } መ.

-----------36. 8 ሰዎች በ3 ቀናት የሚጨርሱትን ሥራ በተመሳሳይ ፍጥነት የሚሰሩ 12 ሰዎች በስንት ቀን ይጨርሱታል?

ሀ. 4 ለ.2 ሐ. 4 መ.6

37. በተሰጡት ቁጥሮች መሰረት ሰንጠረዦቹን ሙሉ

ሀ. ቀ = ሸ

ሸ	ቀ
4	
	3
	15
8	

ለ. ሸ =

ሸ	ቀ
	8
	0.2

ትዕዛዝ ሶስት፡- <u>(Work Out) ሰርታችሁ አሳዩ</u>

38. የአንድ ያልታወቀ ቁጥር እጥፍ በ12 ሲያንስ ውጤቱ 18 ቢሆን ቁጥሩን አግኙ

39. 3ሸ^2+5ሸ -17+6ሸ -ሸ^2+20 በማቃለል ግለፁ

40. ሸ - ዕውን ስብስቡን በመቁጠሪያ ቁጥሮች መስሪያ ክልል ፈልጉ

41. በ "ሸ" ውቅር ላይ የሚገኙ ቢያንስ 3 ጥንዶችን ጥቀሱ

የ6ኛ ክፍል ህብረተሰብ ት/ት የ2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

I.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክል የሆውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን “ሀሰት” በሉ፡፡

----------1. ጣና ሀይቅ የሚገኘው በሰምጥ ሸለቆ ውስጥ ነው፡፡

-----------2. በምስራቀ አፍሪካ የህዝቡ አሰፋፈር ከቦታ ቦታ ይለያየል፡፡

-----------3. ባህል ሰዎች ከአካባቢያቸው የሚማሩትና የሚጋሩት የአኗኗር ዘዴ ነው፡፡

-----------4. በሁሉም ስፍራ ተመሳሳይ እፀዋት ሊኖር ይችላሉ፡፡

-----------5. የኤርትራ ዋና ከተማ አሳይታ ትባላለች፡

-----------6. የእርከን ስራ አፈርን ለመንከባከብ ከጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው፡፡

-----------7. ብክለተ በአየትና በውሃ በካዮች አማካኝነት ይከሰታል፡፡

-----------8. የከርሰ ምድር እንፋሎት የፍል ውሃ አካል ነው፡፡

-----------9. ጠድና ዝግባ የዝቅተኛ ስፍራዎች ናቸው፡፡

---------10. የንከል በረሃ የሚገኘው በአሶስ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡

---------11. የመሬት ቅርፅ ሞላላ ክብ ነው

---------12. የህዝብ አሠፋፈር ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡

---------13. ኒያላ የተሳለው ብርቀየ እንስሳ የተሳለው በሰሜን ተራራ ፖርክ ይገኛል፡፡

---------14. የኤኪሱሞ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በግብርና ነው፡፡

የ6ኛ ክፍል 2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

---------15. የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት 5 ናቸው።
---------16. ድንቅነሽ /ሉሲ/ የምትገኘው ሐዳር በተባለ ሥፍራ ነው።
---------17. የአክሱም ሀውልት የሚነኘው በአፋር ክልል ነው።
---------18. ዘመድ ወይም በትውውቅ የሚደረግ የሥራ ቅጥር ሙስና አይባልም።
---------19. ትንሿ ሀገር በአፍሪካ ቀንድ ሶማሊያ ትባላለች።
---------20. ኦሮሞዎች የገዳ ስርዓት ተከታዮች ነበሩ።
---------21. ሙካሬብ የጥንት ነገስ መጠሪያ ነው።
---------22. ወቅት የመሬት ዙሪት ውጤት ነው።

የሚከተሉትን ጥያቆዎች በማንበብ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።

--------21. የምስራቅ አፍሪካ ኢኮኖሚ የተመሠረተው በ------- ላይ ነው።
ሀ.በንግድ ለ. በኢንዱስትሪ ሐ. በቱሪዝም መ. ግብርና
---------22. ማሳይማራ ፓርክ የሚገኘው በ------------ ሀገር ነው።
ሀ.በኬንያ ለ.በጅቡቲ ሐ.በዩጋንደ መ. በኢትዮጵያ
---------23. ከሚከተሉተ እነስሳት መካከል ደአደጋ የተጋለጠው ---------- ነው።
ሀ.ዝሆን ለ.ነብር ሐ. አንበሳ መ.ሀናለ
--------24. ከሚከተሉት ውስጥ ስጋ በል እነስሳ የቱ ነው
ሀ.አንበሳ ለ. አቦሸማኔ ሐ. ቀበሮ መ. ሁሉም
-------25. ጐሪላ ዝንጀሮ የሚገኘው በ-------------- ሀገር ነው።
ሀ.በዩጋንዳ ለ. በሩዋንዳ ሐ. በታንዛንያ መ. ሀናለ
-------26. የጅቡቲ ዋና ከተማ -------------- ይባላል"፡
ሀ.ጅቢቲ ለ. ካርቱም ሐ.ናይሮቢ መ.ሀናለ
-------27.በባሌ ተራራ የሚገኘው ብርቀዬ እንስሳ --------- ይባላል።
ሀ.ኒያላ ለ. ዋልያ ሐ. ቀይ ቀበሮ መ. ጐሬላ
-------28. ከሚከተሉት እፅዋት መካከል የበረሃ እፅዋተ የቱ ነው?
ሀ.የቁልቋል ዛፍ ለ. ሾላ ሐ. ጥድ መ. ዝግባ
--------29. ከሚከተሉት ውስጥ ሳር በለ እነስሳ --------------- ነው።
ሀ.ቀጭኔ ለ. ዝሆን ሐ. የሜዳ ፍየል መ. ሁሉም
II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አበራሩ
-------30. አድጥድ ማለት ምን ማለት ነው

የ6ኛ ክፍል የስነ-ዜጋ ት/ት የ2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች

ትእዛዝ አንድ፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ለሆነው "እውነት " ትክክል ላልሆነው "ሐሰት" በማለት መልሱ።

-----------1. የቁጠባን ባህል ማዳበር ተቀማጭ ገንዘብ እንዲኖር ያደርጋል።
-----------2. በራስ መተማመን ራስን ከመቻል ጋር ግንኙነት የለውም።
-----------3. ጥገኛ ሰው የራሱን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት በራሱ ማሟላት ይችላል።
-----------4. ሳይሰሩ መብላት የሚበረታታ ተግባር ነው።
-----------5. አንድ ሰው ሳይበደር ህይወቱን መምራት ይችላል።
-----------6. ጠንካራ የስራ ባህል ለልማት መሠረት ነው።

ትእዛዝ ሁለት ፡- ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

-----7. የሙያ ስነ-ምግባር መጓደል በዜጐች ላይ የማያደርሰው ችግር ምንድን ነው?
ሀ. ባለሙያው ሙያውን የበለጠ ለማዳበር ፍላጐቱ ይቀንሳል
ለ. ባለሙያው ውጤት አያገኝም

ሐ. ባለሙያው የራሱንና የቤተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል አይችልም
መ. ሁሉም

-----8.የአንድ ህዝብ ማህበራዊ ችግር የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. ጠንካራ የስራ ባል ለ. ለመና ሐ. እኩልነት መ. መልስ የለም

------9. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የግብርና ስራ አይደለም፡፡
ሀ. ከብት ማድለብ ለ. የማእድን ቁፋሮ ሐ. እርሻ መ. ሁሉም

----10. --------- የራሱ የሆነ ልዩ እውቀትንና ችሎታን የሚጠይቅ የስራ አይነት ነው፡፡
ሀ. ሙያ ለ. የሙያ ችሎታ ሐ. የሙያ ስነ-ምግባር መ. መልስ የለም

----11. ራስን የመቻል ጠቀሜታ ያልሆነው የትኛው ነው?
ሀ. የራስን አመለካከት ለመውሰድና ለመወሰን ያስችላል
ለ. ጥገኛ ያደርጋል
ሐ.በራስ ለመተማመን ይጠቅማል
መ. የእኩልነት ስሜትን ይፈጥራል

----12. ስለ ጥገኝነት እውነት የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. ባለን አቅም እንዳንጠቀም ያደርጋል
ለ. ለራሳችን ክብር እንዳይኖረን ያደርጋል
ሐ. ነፃነታችንን ለሌሎች አሳልፈን እንዳንሰጥ ያደርጋል
መ.ሁሉም

----13.የኮንትሮባንድ ንግድ ጉዳቱ ምንድን ነው?
ሀ. ጥራቱን የጠበቁ ምርቶች እንዲገቡ ያስችላል
ለ. ባህል ተፃፃሪ የሆኑ ፊልሞች አንዲገቡ ያደርጋል
ሐ. ጥራት ያላቸው መድሀኒቶች እንዲገቡ ያደርጋል
መ. መልስ የለም

----14. ከሚከተሉት አንዱ በራሱ የሚተማመን ዜጋ መገለጫ ነው?
ሀ. የሌሎችን አስተሳሰብ በነፃነት ያስተናግዳል
ለ. ስህተቶችን አምኖ ለመቀበልና ለማረም ዝግጁ አይደለም
ሐ. የሌሎችን አመለካከት አይቀበልም መ. ሁሉም

---15. ራስን ለመቻል
ሀ. ታዋቂ ሰው መሆን ያስፈልጋል
ለ. ተገዶ መስራት ያስፈልጋል
ሐ. በእውቀት ራስን ማበልፀግና ማጠናከር ያስፈልጋል
መ. ሀናለ

----16. የቁጠባ ጠቀሜናታ የሆነው የትኛው ነው?
ሀ. ያልተሰበ ችግር ሲያጋጥም ለመቋቋም
ለ. መሠረታዊ ፍላጐቶችን ለማሟላት
ሐ. በትምህርት ራስን ለማሳደግ
መ. ሁሉም

----17. የቁጠባን ባህል የሚፃረር የትኛው ነው?
ሀ. ከአቅም በላይ ለሠርግ መደገስ

ለ. እቁብ ሐ. እድር መ. ሁሉም

---18. ከሚከተሉት አንዱ ስለ ድህነት እውነት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ስብዕናን ይነካል ሐ. የሚወዱትን ያሳጣል

ለ. ክብርን ያሳጣል መ. ሁሉም

----19. ድህነት እንዴት ይመጣል?

ሀ.የቁጠባ ባህልን በማዳበር

ለ. በብኩንነት

ሐ. በአቅማችን መኖር ስንችል

መ. ለ & ሐ

ትእዛዝ ሶስት ፡- በ"ለ" ስር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ስር ካሉት ጋር አዛምዱ።

"ሀ"	"ለ"
-------20. የጋን መብራት	ሀ. ፈተና ኮርጆ የሚሰራ
-------21. ራሱን ያልቻለ ተማሪ	ለ. የሚያውቁትን ለሌሎች ማሳወቅ
-------22. ስለራሱ ትክክለኛ ግንዛቤ ያለው	ሐ. እውቀቱ ለሌሎች የማይተርፍ
-------23. እውቀትን መጋራት	መ. በራሱ የሚተማመን
------24. ብኩንነት	ሠ. ገንዘብን ያለ እቅድና ያለአላማ ማጥፋት

ትአዛዝ አራት ፡- ባዶ ቦታውን ሙሉ።

25. ድንበር እየጣሱ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና ከሀገር ማስወጣት ---------------- ይባላል፡

፱ኛ ክፍል 2ኛው/ወ/ት/ት መለማመጃ ጥያቄዎች